# መቆጠብ ለምን ተቸገሩ?

===============

የቁጠባ አስፈላጊነት ያልገባው፣ ቢያንስ ያልሰማ አለ ማለት ከእውነታው መራቅ ይሆናል። ቁጠባ በአንድ ግለሰብ የገንዘብ አያያዝ ስርአት ውስጥ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ብዙዎች ግን ለመቆጠብ ሲቸገሩ ይታያል።

ቁጠባ ሀብት የመፍጠሪያ እንዲሁም የደስታ እና የብልፅግና ኑሮን ለመምራት አንዱና ዋነኛው መንገድ ሆኖ ሳለ አብዛኞቻችን ግን ቁጠባን ቸል ስንል እንታያለን።

መቆጠብ አለመቻል እንደ ትልቅ ችግር ሊታይ ይገባል። ምክንያቱን ለይቶ መፍትሄውን መፈለግም ጊዜ ሊሰጠው አይገባም።

በህይወታችን ወስጥ ስኬት እና ደስታን የሚያጎናጽፈንን መንገድ ለመጀመር ምንጊዜም አይዘገይም፣ ቁጠባን በተመለከተም ይህ እውነት ነው።

‘መቆጠብ አልችልም’ ከሚለው አመለካከት ይውጡና ለመቆጠብ የተቸገሩባቸውን ምክንያቶች ለይተው በማስወገድ በቁጠባ የብልፅግና እና የደስታ መዳረሻ መንገድዎን ይጀምሩ።

ከሚከተሉት መካከል እርስዎም ላይ ላለመቆጠብ መሰናክል የፈጠሩ ምክንያቶች ይኖራሉና ልብ ይበሏቸው፤ መፍትሄም ይስጧቸው።

### 1. መርሳት ወይም ትኩረት አለመስጠት

መርሳት ወይም ትኩረት አለመስጠት ላለመቆጠብ አንዱ ምክንያት ሲሆን፣ የቁጠባን አስፈላጊነት በአግባቡ ተረድቶ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለመቆጠብ ቁርጠኛ መሆን ይገባል።

### 2. የሚቆጥቡለት አላማ/ግብ አለማስቀመጥ

ለመቆጠብ የተለየ አላማ ወይም ግብ አለማስቀመጥ ያለመቆጠብ አንዱ ምክንያት ነው። በቁጠባችን ልናሳካው የምንፈልገውን አላማ ወይም ግብ ማስቀመጥ ለመቆጠብ ተነሳሽነትን ይፈጥራል።

### 3. መጠን አለማስቀመጥ

በቁጠባችን ልናሳካ ያሰብነውን አላማ ወይም ግብ ማስቀመጥ እንዳለብን ሁሉ ምን ያህል ገንዘብ ቆጠበን ማጠራቀም እንዳለብንም ማቀድ ቁጠባችንን በተገቢው ለማስኬድ ይረዳናል። መጠን ካላስቀመጥን በሂደት ቁጠባውንም ወደመተው ሊያመራ ይችላል።

### 4. በጀት አለመስራት

በጀት ሳይኖር በዘፈቀደ ወጪ የምናወጣ ከሆነ ቁጠባ ላይ እንቀፋት ይፈጥራል። የምናገኘውን ገቢ በአግባቡ መበጀት ወጪያችንን ለመቆጣጠር ስለሚረዳ መቆጠብ ያስችለናል።

**5. ገንዘብን ማባከን**

ብዙም ጥቅም ለሌላቸው ጉዳዮች የምናወጣው አላግባብ የሆነ ወጪ ላለመቆጠብ ምክንያት ይሆናል። ቢቀሩ የማይጎዱንን ወጪዎች ለይቶ ወጪን በመቆጣጠር ለቁጠባ የሚተርፍ በቂ ገንዘብ ማግኘት ይቻላል።

**6. በቂ ገንዘብ (ገቢ) የለኝም ብሎ ማሰብ**

ብዙዎች ላለመቆጠባቸው 'በቂ ገንዘብ የለኝም' የሚል ምክንያት ይሰጣሉ። ይህ ደካማ ምክንያት ነው። አግባብ ባለው የወጪ በጀት እና ስርዓት ባለው የኑሮ ዘይቤ ምንጊዜም ቁጠባን ማካሄድ ይቻላል። የሚቆጠበው መጠን ትንሽ ቢሆንም ትንንሽ ጠብታዎች ውቅያኖስን እንደሚፈጥሩ ማስታወሱ ይበጃል።

**7. በእዳ መዘፈቅ**

በእዳ ተዘፍቆ ገቢን እዳ ለመክፈያ ማዋል ላለመቆጠብ ሌላው ችግር ነው። ቢቻል ከእዳ በመራቅ፣ ግዴታ ከሆነም አላስፈላጊ ወጪዎቻችንን ሁሉ በመለየት ለእዳ ክፍያው በማዋል መቆጠብ መቻል አለብን።

**8. የዋጋ መናር**

የመሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች፣ የአገልግሎት እና ሌሎች የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ዋጋ ንረት ቁጠባችን ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል። ቁርጠኝነቱ ካለ ግን አሁንም የአግልግሎት እና ሌሎችንም ፍጆታዎቻችንን መጠን በመቀነስ እና ዋጋቸው የቀነሱ ቁሳቁሶችን በመግዛት መቆጠብ እንችላለን።

**9. ለጡረታ ጊዜ ከወዲሁ አለማቀድ**

የጡረታ ጊዜዎን አስበው ከወዲሁ መቆጠብ አስፈላጊ ነው።

**10. የአገልግሎት ክፍያን በወቅቱ አለመፈፀም**

በወቅቱ ባልተከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች ሳቢያ የሚደርስ መቀጮ ልንቆጥበው ይገባን የነበረ ገንዘብን ይቀንስብናል።